# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

**ኢትዮጵያችን ልዩ ዕትም ቅጽ 1 ቁጥር 1** **የካቲት ፲፩ ቀን ፪ ሺህ ፱ ዓ.ም.**

## የካቲት 1929 እና 1966

የየካቲት ወር በሀገራችን ኢትዮጵያ ላቅ ያለ ታሪካዊ ቦታን የያዘ ነው። እራቅ ብለን የካቲት 12 ሺህ 9 መቶ 29 ሲታወስ አካፋና ዶማ፣ ፋስና መጥረቢያ ለሰው ልጅ መጨፍጨፊያ ውለዋል። አዛውንት እናትና አባቶች ሕጻናትን ጨምሮ በመኖሪያቸው በእሳት ጋይተዋል። ዋይታና ጩኸቶች፣ የሰቆቃ ድምጾች እሪታና ጣር እያሰሙ ንጹሐን ዜጎች በየመንገዱ፣ በየጉራንጉሩ፣ በየመንደሩ ተዘርግተዋል። በአዲስ አበባ በትንሹ ወደ 30 ሺህ ኢትዮጵያውያን በግራዚያኒ ተጨፍጭፈዋል። እነሆ የካቲት 12 የሰማዕታት ቀን በየዓመቱ ሲዘከር፣ ሲታወስ 80 ዓመት ሞላው። እኛም "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" ክብር ለሰማዕታት ወገኖቻችን፣ ኢትዮጵያ በእናንተ ደምና አጥንት ተጠብቃለች እያልን ሰንደቃችንን ዝቅ አድርገን እንዘክራቸዋለን።

ከየካቲት 12 ዋይታ 37 ዓመታት አስከትሎ የዛሬ 43 ዓመት ሌላ ጩኸት! ስለ መብት፣ ስለ ሀገር፣ ስለ ረሃብ፣ ስለ ድንቁርና አቤት! የተባለበት ጩኸት። አዲስ አበባ በታክሲ አሽከርካሪዎች፣ በመምህራን፣ በሠራተኞች፣ በእስልምና እምነት ተከታዮች፣ በወጣቶች፣ በተማሪዎች፣ በወታደሮች በጥቅሉ በሕዝባዊ አብዮት ተናወጠች። መሬት ለአራሹ፣ የዴሞክራሲ መብት፣ የሃይማኖት እኩልነት፣ የብሔሮች እኩልነት፣ የሴቶች እኩልነት ከፍ ተደርገው ተጮኸላቸው፣ ተዘመረላቸው። ልክ የዛሬ 43 ዓመት የካቲት 11 ቀን 1966 ዓ.ም. የፈነዳው እሳተ ጎመራ አድማሱን አስፍቶ ኢትዮጵያ ለዘመናት የተዳደረችበትን የዘውድና የአፄ ሥርዓት የገረሰሰበት ሕዝባዊ አብዮት ትውስታ። "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" የየካቲት 66ን ሕዝባዊ አብዮት በሀገራችን የትግል ታሪክ ላይ ጥሎ የሄደውን ትውስታ እንቃኛለን።

### *የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም.*

ፋሺስት ኢጣሊያ ዐድዋ ላይ ድል ከተመታች 41 ዓመታት በኋላ የቋጠረውን ቂም በዘመናዊ መሣሪያ ተሸክሞ የመጣው በማርሻል ሩዶልፍ ግራዚያኒ የሚመራው ጦር ከየካቲት 12 እስከ የካቲት 14 ባሉት ሦስት ቀናት ከሠላሳ ሺህ በላይ የሚገመቱ ኢትዮጵያውያንን ፈጀ። ለዕልቂቱና ለግድያው መለያው ኢትዮጵያዊ መሆን ብቻ ነበር። በአዲስ አበባ ከተማ በየመንገዱ የተገኙት ተጨፈጨፉ፣ በየቤታቸው ያሉት በተርከፈከፈ ቤንዚን እሳት ተለቀቀባቸው። ሰማይ በሀዘን ጭስ ጨለመች፣ ምድር በደም ታጠበች። የሰውን ልጅ ጭካኔ ሥልጣኔ አይገታውምና ፋሺስት ኢጣልያ መድፍና መትረየሱን ንጹሃን ላይ አርከፈከፈ። አካፋና ዶማ የሰውን ልጅ አረሱት። ፋስና መጥረቢያ ኢትዮጵያውያንን ቀላ።

የስድስት ኪሎ የያኔው ቤተመንግስት የአሁኑ ዩንቨርስቲ ከአዲስ አበባ በግድም በውድም በተሰበሰቡ በአብዛኛው ሴቶችና ሕፃናት ተሞላ። እብሪት የተሞላበት የግራዚያኒ ንግግር ተጀመረ። በንቀት ያየው ሕዝብ ላይ ስለ "ታላቂቱ ጣልያን" መደስኮር ጀመረ። ግን ብዙ አልቆየም አብርሃም ደቦጭና እና ሞገስ አስገዶም ቦንቦችን አከታትለው ወረወሩበት። ግራዝያኒ ቆሰለ፣ የአየር ኃይሉ ኃላፊ ተገደለ። አብርሃም እና ሞገስ በቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስትያን በኩል ባለው የቤተመንግስቱ የጋራ አጥር ዘለው ወጡ እና ታክሲ ይዞ ወደሚጠብቃቸው ስምዖን በመገስገስ አመለጡ።

ወርሃ የካቲት ከማይዘነጋባቸውና ከሚታወስባቸው ነገሮች መካከል አንዱ በየካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም የተከሰቱት መራራ የጽልመት ቀናት ናቸው፡፡ በነዚህ ቀናት ውስጥ ለኢትዮጵያውያን የተደገሰው የሞት ድግስ እጅግ ዘግናኝና ኢ-ሰብአዊም ነበረ፡፡ መነሻዎቹ ሁለት ናቸው፤ ለአርበኝነት ሙያ ወደ ደቡብ ዘምቶ የነበረውን የራስ ደስታ ጦር ለመምታት በርካታ ጦር አስከትሎ ሄዶ የነበረው ማርሻል ግራዚያኒ ሞቷል ተብሎ ወሬ የሚናፈሰው ሲሆን ሌላውና ዋናው ዳፋ ደግሞ፤ በየካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም. በገነተ ልዑል ቤተ-መንግስት መግቢያ በር፣ በረንዳ ላይ በማርሻል ግራዚያኒ ላይ በአብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም አማካይነት የመግደል ሙከራ ስለተደረገበት መሆኑ በታሪክ ፀሐፊዎች ተዘግቧል።

ከየካቲት 12 እስከ የካቲት 14 ቀን 1929 ዓ.ም የተፈጸመው ጭፍጨፋ በንጹሃን ላይ የተፈጸመ ግድያ ነው፡፡ ሰላማዊያኑ ኢትዮጵያዊያን በግፍ ዕልቂት የተፈጁበት ይህ ዕለት ዐርብ 1929 ዓ.ም. ነበር፡፡ ረቡዕ የካቲት 10 ቀን 1929 ዓ.ም ግራዚያኒ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ፡፡ ለሕዝቡም ሞተ ተብሎ የተወራው ስሕተት እንደነበረና ምንም ያለ መሆኑን ለማሳየት፣ ለማረጋገጥ ስለፈለገ በማግሥቱ የካቲት 11 ቀን 1929 ዓ.ም በዛሬው የየካቲት 12 አደባባይ ላይ እንዲሰበሰቡ አስደረገ፡፡ ሆኖም የተሰብሳቢው ቁጥር ስላነሰበትና ያሰበውን ያህል ትኩረት እንዳለገኘ ስለተሰማው፣ በማግሥቱ ዐርብ የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ከቤተ ክርስቲያን ቅዳሴ መልስ ልክ ከጥዋቱ በ4፡00 ሰዓት ሕዝቡ በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ፊት ለፊት እንዲሰበሰብ አዘዘ፡፡ ለነዲያንና ለችግረኞችም ብዙ ሊሬ እንደሚሰጥ ጭምር አስለፈፈ።

የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም. ልክ በአራት ሰዓት ይጀመራል የተባለው ፕሮግራም ግብጻዊው አቡን፣ አቡነ ቄርሎስ ታምሜያለሁ ብለው ስለቀሩ፣ ስለዘገዩ እስከሚመጡ ድረስ ለአንድ ሰዓት ያህል ዘገየ፡፡ ወታደር ተልኮ አበኑ ልክ 4፡55 ሰዓት ቤተ መንግሥት ደረሱ፡፡ ወንበር መጥቶላቸው ከግራዚያኒ በስተቀኝ በኩል ከከፍተኛ የፋሺስት ባለስልጣናት ጎን ተቀመጡ፡፡ ከግራዚያኒም በስተግራ በኩል ጀኔራል ጋሪባልዲ፣ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሳ፣ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት ከሌሎች ባንዶች ጋር ተቀምጠው ነበር፡፡ ስብሰባው እንደተጀመረ ግራዚያኒ ሻኛው እንዳበጠ ኮርማ ቁና ቁና እየተነፈሰ ኢትዮጵያውያንን ያበሻቅጥ ጀመር። “ይኼው አለሁ!... ሞቷል እያላችሁ የምታወሩትና የምታስወሩት ሁሉ ከንቱ ሟርት ነው፡፡” እያለ የኢትዮጵያን ሕዝብ በገዛ ሀገሩና በገዛ መሬቱ ላይ እያዋረደ ይደነፋ በነበረበት ወቅት በማከታተል ቦንቦች እነአብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም ካሉበት ደርብ ላይ ተወረወሩ፡፡ የመጀመሪያው እንደተመረወረ ብዙዎቹ የመሰላቸው ለስብሰባው ማድመቂያ መድፍ የተተኮሰ ነበር፡፡ ሁለተኛው ሲወረወር ግን፣ አቡነ ቄርሎስና ግራዚያኒ መሬት ያዙ፡፡ በስተ ግራ በኩል ያሉትም ሁለት ጥበቃዎች ወዲያውኑ ሞቱ፡፡ ሦስተኛው ሲወረመርም ግራዚያኒ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሊገባ ፊቱን አዙሮ መሸምጠጥ ጀምሮ ነበር፡፡ ሆኖም፣ የሦስተኛው ቦንብ ፍንጣሪዎች በርካታ ቦታ አቆሠሉት፡፡ በፍጥነት ወደ ኦስፒዳሌ ኢታሊያኖ (የጣሊያን ሆስፒታል) የዛሬው “ራስ ደስታ ሆስፒታል” ወሰዱት፡፡

ይህን አስታኮ የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም. እኩለ ቀን ጀምሮ እስከ የካቲት 14 ቀን 1929 ዓ.ም. ምሽት ድረስ ከሰላሳ ሺህ በላይ ኢትዮጵያዊያን በግፍ ተፈጁ፡፡ ብዙ ጊዜ የሚነገረው ቁጥር በአዲስ አበባ ብቻ የተፈፀመውን ግድያ የሚያሳይ ነው፡፡ በፋሺስቱ ግራዚያኒና በግብረ አበሮቹ፣ በከሃዲ ባንዳ ኢትዮጵያውያን ትብብር እመላው ኢትዮጵያ አውራጃችና ቀበሌዎች ባልቴት፣ ሽማግሌ፣ ሕፃን፣ ወጣት፣ ካሕን፣ ሴት፣ እስላም፣ ክርስቲያን፣ ማንም ከማንም ሳይለይ ተፈጀ፡፡

አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የነበሩትና በወቅቱ በስፍራው የነበሩት አሃዱ ሳቡሬ በየካቲት 12 ቀን 1947 ዓ.ም እንደገለጹት፤ “ኢትዮጵያን መሬቷን እንጂ ሕዝቧን አንፈልግም” በሚል ዘረኛነት የፈጀውና ያስፈጀው ግራዚያኒ፤ በከተማ ነዋሪ የነበሩትን ኢትዮጵያውያን እርጉዝና ሽባዎችን ሳይቀር ነበር ያስፈጃቸው፡፡ ግድያው በመትረየስና በጠመንጃ ብቻ አልነበረም፡፡ በአካፋ ተጨፍጭፈው፣ በዶማም ተፈልጠው፣ በፋስና በመጥረቢያም ተቆራርጠው የሞቱትን ቤቱ ይቁጠራቸው፡፡ ከቤታቸው ለመውጣትና ለማምለጥ ያልቻሉትን ባልቴቶችና ሽማግሌዎችም ቤቱን የኋሊት እየዘጉባቸው ነበር እሳት ጎጇቸው ላይ የለኮሱባቸው፡፡

በዚህ ለሦስት መዓልትና ለሦስት ሌሊት ሲፈጸም በነበረው ግፍ ወቅት፤ የኢትዮጵያውያኑ ሰማዕታት አስክሬን በገዛ አገሩ ጥርኝ አፈር ተነፍጎ በየጎዳናው ተዘርሮ፣ ደሙም እንደ ሐምሌ ጎርፍ ሲጥለቀለቅ፣ በገዛ ቤታቸው የተቃጠሉትና የቤቱ ቃጠሎ ነበልባል ደግሞ ጢስ እስከ ሰማይ ሲያርግ ያዩ የዐይን ምስክሮች ዛሬም አሉ፡፡ በአራተኛው ቀን የካቲት 15, 1929 ዓ.ም. ሁኔታዎች ጋብ ያሉ መሰሉ፡፡ የግራዚያኒም ቁጣ የበረደ መሰለ፡፡ ለከተማዎቹም ጽዳት ሲባል የሰማዕታቱ አስክሬን አፈር እንዲቀምስ ተደረገ፡፡ ብዙዎቹ በቡልዶዘር አማካይነት በጅምላ ተቀበሩ፡፡ እነዚህ የጅምላ መቃብሮች አብዛኞዎቹ ዛሬም በቅጡ አይታወቁም፡፡ የተወሰኑት ግን ለዓጽማቸው ማረፊያና መታሰቢያ ተብሎ በቅድስት ሥላሴ ሃውልት ቆሞላቸዋል፡፡

አብርሃም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም ከራስ አበበ አረጋይ የአርበኞች ጦር ጋር ከተቀላቀሉ በኃላ ራስ አበበ አረጋይ ልዩ እንክብካቤ እንዲያገኙ አደረጉ። ቆይተው ግን የነበራቸውን የትምርት ደረጃ በመረዳት ከሀገር ውጭ ወጥተው ለሀገራቸው ቢሰሩ ይጠቅማሉ ብለው በማሰብ ከስንቅ እና ገንዘብ ጋር ወደ ሱዳን እንዲሄዱ መከሯቸው። ሆኖም ግን በጉዞአቸው ላይ ሱዳን ሊገቡ ትንሽ ሲቀራቸው ፎቶዋቸው በገጠር ባሉ የፋሺሽት ወታደሮች ሁሉ ተናኝቶ ነበርና በፋሺስቶች ተይዘው በስቅላት ሰማዕት ሆኑ። በኋላ ግን አፄ ኃይለሥላሴ በሱዳን በኩል ጣልያንን ከእንግሊዝ ሰራዊት ጋር ሆነው ድል ሲያደርጉ የአብርሃም እና የሞገስ አስከሬን ተቆፍሮ ወጥቶ አሁን አዲስ አበባ በሚገኘው የቅድስት ስላሴ አርበኞች ሐውልት ስር እንዲያርፍ አድርገዋል። ለወራሪ ፋሽስት አንገዛም ባይነታችሁን፣ ጀግንነታችሁን ታሪክ ሲዘክረው ይኖራል።

### *ወርሃ የካቲት 1966 ዓ.ም.*

የዚህ ዓለም ፍጥረት ሰው የሰራውም ይሁን እግዚአብሔር የፈጠረው ከጣት ጣት አንዲሉ፡ አንዱ ካንዱ በልጦ ብቅ ይላል። ይህም መበላለጥ ፈጣሪ ዕፍ ያለባቸው ባለነፍስ ብቻ ሳይሆኑ ያላለባቸውም ግዑዛን በዚህ ህግ የመበላለጥ፣ አንዱ ካንዱ ደምቆ የመታየት ዘይቤ አላቸው።

ሰለሆነም በአሜሪካ ሚያዚያ (April 1775)፣ በፈረንሳይ ግንቦት (May 1789)፣ በራሽያ ጥቅምት (October 1917)፣ በኢትዮጵያ የካቲት (February 1974) የአብዮት ነውጥ የፈነዳባቸው በመሆን ከሌሎች ወራቶች ደምቀው ታይተዋል። ወደ ታሪክ ሕያውነትም አልፈዋል።

የኛው የ66ቱ የካቲት አብዮትም የኢትዮጵያን መንግስት ኃይለኛ ዓውሎ ንፋስ እንደመታው ያልታደለ ከተማ፤ የታቹን ወደ ላይ፡ የላዩን ወደታች አድርጎ፤ አፈር ድሜ አስግጦ ያደባየ እና ምስቅልቅሉን ያወጣ በኢትዮጵያ መልክዐ ምድር ከሁለቱ የጣሊያን ወረራ ቀጥሎ በሀይለኛነቱ፣ በታሪክ ዕምቅነቱ፣ በደማቅነቱ ወደር የማይገኝለት ትልቁ ታሪካችን ነው።

የ66ቱ አብዮት ትልቅነቱ የታሪክ ደማቅነቱ ብቻ ሳይሆን የቀሰቀሰው ሹም ሽር የኢትዮጵያን መንግስት መሪን ከተመሪው፣ ሰራተኛን ካሰሪው፣ ሹሙን ከምንዝሩ ሳይለይ እንደ ካርታ የጦወዘ፣ ብዙ ነጻ አውጪ ነኝ ባይ የወለደ፣ ያገሪቱንም የቆዳ ስፋት የቀነሰ ትልቁ ደፍራሳ  ታሪካችን ነው ተብሎ በሙሉ አፍ ቢነገር ንስሃን የሚጠይቅ ትዝታ አይሆንም።

ዛሬ ይህ የ43 ዓመት እድሜ ያስቆጠረው የካቲት 66 አብዮት በአዎንታዊም ይሁን በአሉታዊ ቆንጠጥ ያረገን ሁሉ በወርሃ የካቲት በውስጣችን ካለው የአዕምሮ ቴፕ ላይ በደስታም ይሁን በትካዜ እንደ ሲኒማ በየሀሳብ ሰሌዳችን ላይ ከነቀለሙ መታየቱ አይቀሬ ነው።

ይህ ከኢትዮጵያ ወሮች 6ኛ ከሆነው የካቲት ወር የአብዮት ፍንዳታ ላይ ለመድረስ በሀገራችን ዘርፈ ብዙው ህዝብ (በሃይማኖት፣ በዘር፣ በቋንቋ፣ በነገድ) ልዩነትን አጉልቶ ሳያሳይ በህብረት አንዴም በአዎንታቸው፡ ሌላ ግዜም በአሉታቸው በትግል ለውጥን ሲሻ አልፉዋል።

የቀዳመዊ አፄ ኃይለሥላሴ ስነ መንግስት ከጅምሩ የሰራቸው ጥሩ ጥሩ የአስተዳደር ለውጦች በወንድማማቾቹ ጀነራል መንግስቱና ግርማሜ ነዋይ ለውጥ የመሻት ዓመጽ የአፄ ኃይለሥላሴ መንግስት የሰራው አዲስ ሥራ እርጅና እንደገባቸው ቢጠቁምም የዚህን የለውጥ መሻት ምስጢር መልስ ፍለጋ የንጉሱ መንግስት "አንካሴ በሁላሴ" ሲል የለውጡ ሽታ በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በኩል ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ሲደርስ መስመር እየያዘ፣ የፖለቲካ ጥያቄ እየሆነ፤ ይናጥ፣ ይቦካ፣ ይጋገር ጀመር።

ውሎ እያደርም የመሬት ሥሪት ጥያቄ፣ የዲሞክራሲ መብት ጥያቄ፣ የሰራተኛ የመደራጀት መብት ጥያቄ፣ የብሔርና የብሔረሰብ መብት ጥያቄ እና ሌሎችም ጥያቄዎች የዩኒቨርሲቲውን መድረክ ያዙት። አብሮም ከዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች የለውጥ አቀንቃኝ ተዋንያን በአብዛኛው በግዜው ለተነሱት ጥያቄዎች መፍቻ ቁልፍ የ"ግራ ዘመም ርዕዮት" ነው ባዩ እየበዛ፤ በአማራጩ የ"ቀኝ ዘመም" አስተሳሰብ በአድኃሪነት ተፈርጆ ማረፊያ ቤት ተቀመጠ። ይህም የ"ቀኝ ዘመም" ፖለቲካ ለብዙ ዘመን ሳያንሰራራ ቀረ።

እንግዲህ! "ጠንክሮ የተጓዘ ያሰበበት ይደርሳል" እንዲሉ፤ የተማሪው እንቅስቃሴ እና በኢትዮጵያ መንግስት ላይ በሰፊው በሰፈነው ስር የሰደደ ድህነት እና ለተሽካሚ ትከሻ ገሽላጭ የሆነው ጭቆና መንኮርራኩር ሆነው ተማሪውን፣ ለውጥ ፈላጊ ተራማጁን ህዝብ ሰብስቦ፣ በኋላ ወቶአደሩን ጨምሮ ከደረቀ የትግል ምንጭ ወደ ገባር ወንዝ፣ ከገባር ወንዝ ወደ ትልቅ የሞላ የህዝብ ጎርፍነት አድጎ የካቲትን ወር አጥለቀለቀው። ይህንን አዲስ ሁኔታ ማንበብ የተሳነው የአፄ ኃይለሥላሴ መንግስት በግዜው የነዳጅ ባለቤት ሀገሮች በነዳጅ ላይ የጨመሩትን የነዳጅ ዋጋ ለማካካስ በአገሪቱ የነዳጅ ዋጋ በመጨመሩ በየካቲት መግቢያ የዋጋው መጨመር ያበሳጨው ታክሲ ነጂ ድንገት በጫረው የተቃውሞ ጩኸት "የነዳጅ ዋጋ ጭማሬው ህገወጥ ነው" ሰሚ አግኝቶ በአዲስ አበባ ከተማ ትልቅ የተቃውሞ ሰልፍ ሆኖ ዋለ። ልክ የዛሬ 43 ዓመት የካቲት 11 ቀን 1966 ዓ.ም. ።

በመቀጠልም የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ኢትዮጵያውያን በ10,000 በሚቆጠር ህዝብ ወጥተው የሃይማኖት እኩልነት መብት ጥያቄ አነሱ፡፡ ቀጥሎም መምህራን የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ትመህርት አሰጣጥ ግምገማን አስመልክቶ የተቃውሞ ሰልፍ አደረጉ፡፡ የአዲስ አበባና የአካባቢው ህዝብም የ"መሬት ላራሹን" እና ሌላም የወቅቱ ጉዳዮች ላይ መፈክር በማንገብ በሚያረጉት የተቃውሞ ሰልፍ የአዲስ አበባ ከተማን የጦር ቀጠና አስመሰሉት።

ይህን አሻፈረኝ ያለና በየዕለቱ ድካም እና ስጋት ሳያግደው በየቀኑ ተቃውሞ ሰልፍ የሚያረገውን ህዝብ በስጋት የተመለከተው የአፄ ኃይለሥላሴ መንግስት አርጎት በማያውቀው ሁኔታ የካቲት 23 ቀን የነዳጅ ዋጋን ቀነሰ። የማይገሰሰው የማይከሰሰው የአፄ ኃይለሥላሴ መንግስት በ40 ዓመት ዘመኑ ለመጀመሪያ ጊዜ አፈገፈገ።

የፀሐፊ ተዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ጠቅላይ ሚንስቴርነት ከነካቢኔሃቸው ሥልጣኑን ለቆ መጀመሪያ በልጅ እንዳልካቸው መኮንን፣ ቀጥሎ በልጅ ሚካኤል እምሩ የተንገዳገደውን የአፄ ኃይለሥላሴን መንግስት መልሶ ለማቆም ቢሞከርም ሳይሆን ቀረ። በመቀጠልም

ለንጉሱ እረጅም ዕድሜ እየጠየቀ፣ ከአንዳንድ መካሪዎቹ ጋር በመሆን በዙፋኑ ዙሪያ የተሰለፈው የሻለቃ በታች የጦር ኃይሎች ወኪል መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም. በጊዜያዊነትና በሞግዚት አስተዳደር ስም የመንግሥት ሥልጣኑን ጨበጠ። የየካቲቱ 66 ሕዝባዊ አብዮት ወደ ወታደራዊ አብዮት ተሸጋገረ። በሦስት ወር ጉዞውም የንጉሱን 60 ሹማምንት ያለፍርድ ገድሎ የፍየል ወጠጤ ጨፈረ። ንጉሱን ከስልጣን በማውረድ እራሱን ደርግ ብሎ በመሰየም ብቸኛው የኢትዮጵያ መንግስት ሆነ። አማካሪዎቹም በዚሁ ሹምሽር ከስልጣን ተካፋይነት ወደ ሁለተኛ ደረጃ አማካሪት ወረዱ።

ደርግም ለሚቀጥለው 17 ዓመት ኢትዮጵያን ሲያስተዳድር መጀመሪያ “ኢትዮጵያ ትቅደም” በኋላ “ሶሻሊስት ሪፑብሊክ” ፈጠርኩ ቢልም ገና ከጅምሩ ተቃዋሚውን ጸጥ ለጥ አድርጎ ለመግዛት ያወጣው የዴሞክራሲያ መብት እገዳ አዋጅ እያደር ቀውስ ውስጥ ከተተው። ወታደራዊ ባህሪውና ጦረኝነቱ በማርሽና በቀረርቶ ታጀበ።

በዋና ተቃዋሚነት ኢሕአፓ በደርጉ ስርም እነ መኢሶን፣ ወዝ ሊግና ሌሎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጨምሮ በኢትዮጵያ የአብዮት ተውኔት መድረክ ላይ አዋጭ ነው ያሉትን የትግል ስልትና ዘዴ ቢከተሉም “ሽንኩርት የባህሪውን ይሸታል” እንዲሉ የደርግ መንግስት ወታደራዊ ባህሪው አይሎበት ባልተወለደ አንጀቱ የመጀመሪያዎቹን ከርቸሌ ጓሮ፤ የቀጠሉትን በየመንገዱ ዳር ዳር ላይ፤ ከዚህ የተረፉትን በደርግ ጽህፈት ቤት በማነቅ፡ ገሎ ወደ ታሪካዊ ፍርድ ሸንጎ አልፏል።

የደርግም መንግስት በስልጣን ዘመኑ የተነሱትን አበይት ጥያቄዎች ለመመለስ ከሰላም ውይይት ይልቅ ጦር ሰባቂ ጎራዴ ታጣቂ በመሆኑ ኤርትራን አስገንጥሎ፣ የኢትዮጵያን ህዝብ ንብረት አሳጥቶ፣ 1.000.000 ህዝብ ለርሀብ አጋልጦ፣ ከ400,000 እስከ 600,000 ህዝብ ገሎ ለአሁኑ የወያኔ/ኢሕአዴግ ዘረኛ መንግስት ኢትዮጵያን አጋልጦ ካገር ሸሽቶ፣ ፈርጥጦ ሄዷል።

“አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” ከወርሃ የካቲት 1966 ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ትምህርት በመቅሰም ከሕዝብ ብሶትና ስቃይ የተነሳ ገንፍሎ የሚነሳ ግብታዊ እንቅስቃሴ እንዳይቀለበስ ተደራጅቶና ተዘጋጅቶ የተቀናጀ ትግል ማድረግ እንደሚገባ ግንዛቤ መወሰድ ይገባዋል እንላለን።

በ1997 ዓ.ም. የምርጫ ትርዕይት የኢትዮጵያ ሕዝብ ያገኘውን ድል የተጠናከረ የፖለቲካ ድርጅት ቢኖር ዛሬ ኢትዮጵያ የልጆቿ ነበረች። አሁንም በቅርቡ በኦሮሞ፣ አማራና በእስላሙ እብረተሰብ ዘንድ የተነሱ ሕዝባዊ ቁጣዎች የተደራጀና የተጠናከረ የፖለቲካ ድርጅት ቢኖር ትግሉን አመራር እየሰጠና እየተፋለመ የወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ ዘረኛ አገዛዝን በነበር ወደ ታሪካዊ ሥፍራው በተወረወረ ነበር።

የሕዝብንና የሀገርን ጥያቄ ከግብ ለማድረስ የሚቻለው በመላ ሀገሪቱ ዘር፣ ክልልና ሃይማኖት ሳይለይ ሁሉንም ያቀፈ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በተጠናከረ የፖለቲካ ድርጅት ሲመራ ነው። ለዚህም መደራጀት አሁንም መደራጀትና መታገል ዋነኛው አማራጭ በመሆኑ “ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” እንሰባሰብ፣ እንደራጅ እንላለን።

በመጨረሻም በሀገራችን ኢትዮጵያ የነፃነት፣ የአንድነትና የግዛት ሉዓላዊነት ተጋድሎ በደምና አጥንታችሁ ሀገራችሁን ጠብቃችሁ ለዛሬ ላበቃችኋት ጀግኖችና አርበኞቻችን ክብር ለእናንተ እንላለን። በየካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም. በግፍ ለተጨፈጨፋችሁ  ኢትዮጵያውያን ሀገርና ሕዝብ ሁሌም ይዘክሯችኋልና ከእኛም “ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” መዘክራችንን እነሆ! እንላለን። የየካቲት 1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ ሕንቅስቃሴ በአረመኔውና ጦረኛው ወታደራዊ አገዛዝ ተቀልብሶ በ17 ዓመት የግፍ አገዛዝ ያለፍርድ ለተገደላችሁ፣ በየጊዜው በደርግ ጥይት ለተጨፈጨፋችሁ ኢትዮጵያውያን “ታሪካችሁ ህያው ነው” እንላለን። በቀጣይነትም ታሪክ እራሱን ይደግማል እንዲሉ ለዴሞክራሲ መብትና ለሀገር አንድነት ስትሞግቱ፣ ስትታገሉ በዘረኛው የወያኔ/ኢሕአዴግ አገዛዝ እስከ ወዲያኛው ላሸለባችሁ ወገኖች አልረሳናችሁም፣ በግፍ የፈሰሰው ደማችሁ ፍትህ እንደሚያገኝ አንጠራጠርም እንላለን።

የየካቲት 12 ሰማዕታት ሁሌም እንዘክራችኋለን!!!
የካቲት 66 መደራጀትን አስተማሪ ነው!!!

**ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!**
**እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!**
**“አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ”**
የካቲት 11 ቀን 2009 ዓ.ም. (February 18, 2017)

<u>**ዋቢ ማጣቀሻ ፦**</u>

- ሳምንታዊው የአዲስጉዳይ መጽሔት ቅጽ 7፣ ቁ. 152 ፤ የየካቲት 16 ቀን 2005 ዓ.ም::

**ማሳሰቢያ ፡**

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» «***ኢትዮጵያችን***» ልሳን በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org

ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com

ምስለ ገጽ : Ethiopiachen Hagerachen